በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No. 10/752
ቀን / Date 19 መጋቢት 2006

በዝርዝሩ ለተመለከቱት በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- **የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፤**

የገቢ መንገደኞች የስጋት ስራ አመራርን መሰረት ያደረገ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 96/2006 የጸደቀ ስለሆነ በመመሪያው መሰረት እንዲፈጸም እያሳሰብኩ የመመሪያውን 6 /ስድስት/ ገጽ ኮፒ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

በከር ሻሌ ዱሌ
ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለኦፐሬሽን ዲዛይን ፕሮግራምና ልማት ስራዎች ዘርፍ
- ለቅርንጫ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ሥራዎች ዘርፍ
- ለዐቃቤ ህግ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ህግ ተገዥነትና ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ጥናትና ረቂቅ ዝግጅት ቡድን

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

- ለብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት
- ለኢትዮጵያ አየር መንገድ
- ለኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት

<u>አዲስ አበባ</u>

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## የገቢ መንገደኞች የስጋት ስራ አመራርን መሰረት ያደረገ የጉምሩክ ስነ-ስርአት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 96/2006

መጋቢት 2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# የገቢ መንገደኞች የስጋት ስራ አመራርን መሰረት ያደረገ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 96/2006

ወደ አገር የሚገቡ ሁሉንም መንገደኞች እና ዕቃዎችን መፈተሽ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከሃብት አጠቃቀም አንፃርና በአገር ገጽታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ሆኖ በመገኘቱ፣

የሥጋት ሥራ አመራር መርህን በተከተለ መልኩ ከፍተኛ የሥጋት ደረጃዎችን በመለየትና የተመረጡ ስጋቶችን መሠረት ያደረገ ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥና ውጤታማ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ በመሆኑ፣

በዚህም መሠረት በጥናት ላይ የተመሠረተ የመንገደኞችና የዕቃዎች ባህሪ የስጋት ደረጃ በመለየት የሥጋት ሥራ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 112(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ *"የገቢ መንገደኞች የስጋት ስራ አመራርን መሰረት ያደረገ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 96/2006'* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) *"ኤርፖርቶች"* ማለት የጉምሩክ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ኤርፖርቶች/የአየር ወደቦች/ ናቸው፡፡
   2) *"ሥጋት"* ማለት የጉምሩክ ህግን የሚፃረር ማንኛውም ዓይነት አሉታዊ እንቅስቃሴ ወይም ክስተት ነው፡፡
   3) *"የሥጋት ሥራ አመራር "* ማለት በጉምሩክ ክልል በሚገቡና በሚወጡ መንገደኞች እና ዕቃዎች ላይ የአገልግሎት አሰጣጡን እና የቁጥጥር ስርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያዩ የሥጋት ደረጃዎች በማውጣት የሚከናወን አሠራር ነው፡፡



The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Revenues and Customs Authority

4) *"ተመላላሽ መንገደኛ "* ማለት በአገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ኤርፖርቶች በኩል በሦስት ወር አንድ ጊዜ እና ከአንድ ጊዜ በላይ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ውጪ አገር ወይም በአገር ውስጥ የሚመላለስ ማለት ነው፡፡

5) *"ፍተሻ"* ማለት ወደ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤቶች በሚገቡ መንገደኞች እና ዕቃዎች ላይ በሰው እና በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ እና/ወይም በአካል የሚደረግ የመንገደኞች እና የዕቃ ፍተሻ ሂደት ነው፡፡

6) *"ዕቃ"* ማለት ማናቸውም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ግዙፍነት የሌላቸው በሕግ እንደተንቀሳቃሽ ንብረት የሚታወቁትን ንብረቶችና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን በአገልግሎት ላይ የዋሉ የተፈጥሮ ሀይል ውጤቶችንና የከርሰ ምድር ሀብትን የሚያካትት ሲሆን ገንዘብንም ይጨምራል፡፡

7) *"አልፎ አልፎ መረጣ"* ማለት በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ከተለዩና በአረንጓዴ የማለፊያ መስመር ከሚያልፉ መንገደኞች ውስጥ የተወሰነ ቁጥር ያላቸውን መንገደኞች በመምረጥ ፍተሻ እንዲደረግ የሚለይበት ሥርዓት ነው፡፡

8) *"ባለስልጣን"* ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፡፡

9) *"አዋጅ"* ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ዓ.ም ነው፡፡

10) በዚህ መመሪያ ያልተተረጎሙ ሌሎች ቃላት እና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አገልግሎት በሚሰጥባቸው ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል በሚገቡ መንገደኞችና ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የስጋት ደረጃዎች አመዳደብ እና መስተንግዶ</u>

4. <u>*የሥጋት መምረጫ መስፈርቶች*</u>

በመንገደኞች እና ዕቃዎች ላይ የሚደረግ የሥጋት ደረጃ አመዳደብ የሚከተሉትን መስፈርቶች መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ሀ) መንገደኛው የተነሳበትን ወይም የተላለፈበትን አገር /Country of departure or transit/



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

ለ) የመንገደኛውን የኋላ ታሪክ (Passenger profile)

ሐ) መንገደኛው የመጣበትን ምክንያት

መ) የመንገደኛው የተመሳሳሽነት ሁኔታ

ሠ) አልፎ አልፎ መረጣ (Random Selection)

ረ) ከኢንተለጀንስና ከሌሎች ጠቋሚ አካላት በሚገኙ መረጃዎች

ሰ) መንገደኛው በጊዜው የሚያሳየው የተለየ የእንቅስቃሴ ሁኔታ

ሸ) ሌሎች በታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በሚለዩ መስፈርቶች፤

## 5. የሥጋት ደረጃዎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ላይ በተገለፁት መስፈርቶች መሰረት ወደ ኤርፖርቶች የሚገቡ የመንገደኞች እና የዕቃዎች የሥጋት ደረጃ

1) ከፍተኛ የሥጋት ደረጃ /High Risk / እና
2) ዝቅተኛ የሥጋት ደረጃ /Low Risk / ተብሎ ተከፍሏል፡፡

## 6. የማለፊያ መስመሮች /Channels/

1) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 በተከፈሉት የሥጋት ደረጃዎች መሰረት የማለፊያ መስመሮች

   ሀ) ቀይ የማለፊያ መስመር /Red channel/ እና

   ለ) አረንጓዴ የማለፊያ መስመር /Green channel/ ናቸው ፡፡

2) ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የተመደቡ መንገደኞች በቀይ መስመር ማለፍ ያለባቸው ሲሆን በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የተመደቡት መንገደኞች ደግሞ በአረንጓዴ የማለፊያ መስመር ማለፍ አለባቸው፡

## 7. የአገራት / የበረራዎች/ የሥጋት ደረጃ የሚወሰንበት ሁኔታ

1) የአገራት /የበረራዎች/ የሥጋት ደረጃ መንገደኛው የተነሳበትን ወይም የተሳለፈበትን አገር መሰረት በማድረግ በታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጥናት ላይ በተመሰረተ እና የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ በመመልከት ከፍተኛ እና ዝቅተኛ የሥጋት ደረጃ በማለት ተለይቶ በየ 3(ሶስት) ወሩ ለቅ/ጽ/ቤቶች ይተላለፋል፡፡



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ባስተላለፈው የሀገራት የሥጋት ደረጃዎች መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶችም ለመንገደኞች ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

8. <u>*መንገደኞች የመጡበት ምክንያት የሥጋት ደረጃ የሚወሰንበት ሁኔታ*</u>

በመንገደኞች እና በዕቃዎች ላይ ከሚደረግ የሥጋት ደረጃ አመዳደብ መሥፈርት ውስጥ መንገደኛው የመጣበትን ምክንያት መሠረት ያደረገ የሥጋት ደረጃ አመዳደብ እንደሚከተለው ነው፡፡-

*ሀ) በዝቅተኛ የሥጋት ደረጃ የሚመደቡ መንገደኞች፤*

1) በዝቅተኛ ስጋት ደረጃ ላይ ከተመደቡ አገራት ለጉብኝት የሚመጡ
2) ለአህጉር አቀፍና ለአለም አቀፍ ስብሰባ/ለኮንፈረንስ የሚመጡ
3) ነፃ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚመጡ
4) ዲፕሎማቶች
5) ለጥናትና ለምርምር የሚመጡ
6) በመንግስታዊና በግልና ተቋማት ለሥራ ወይም ለአገልግሎት ተጋብዘው የሚመጡ
7) ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን
8) ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አገር የሚመጡ ኢትዮጵያዊያን እና
9) ሌሎች በታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተለይተው በሚወሰኑ መንገደኛው የመጣበት ምክንያት፡፡

*ለ) በከፍተኛ ሥጋት ደረጃ የሚመደቡ መንገደኞች፤*

1) ተመላላሽ መንገደኞች፤
2) ለኤግዚቢሽን ጉዳይ የሚመጡ ፤
3) የተቆጣጣሪ መስሪያቤቶችን ፈቃድ የሚጠይቅ እቃን የያዘ መንገደኛ ፤
4) ነጋዴዎች፤
5) በግል ጉዳይ ከአገር ወጥተው የሚመለሱ እና
6) ሌሎችም በታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተለይተው በሚወሰኑ መንገደኛው የመጣባቸው ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 9. የመንገደኞች እና የዕቃዎች የሥጋት ደረጃ የሚወሰንበት ሁኔታ

1) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 7 እና 8 የተቀመጡት የሥጋት ደረጃ አመዳደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 4 በተቀመጡት ሌሎች የሥጋት ደረጃ አመዳደብ መስፈርቶች በሙሉ ወይም በከፊል ማረጋገጥ በተቻለው መሰረት የሥጋት ደረጃ ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ተብሎ የሚወሰን ይሆናል፡፡
2) በተለየው የስጋት ደረጃ መሰረት መንገደኞች እና እቃዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ በአንቀፅ 10 በተደነገገው መሰረት በዕለቱ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ ላይ በሚመደብ ኢንስፔክተር የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 10. በተወሰነው የሥጋት ደረጃ መሠረት መንገደኞች እና ዕቃዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ

1) ማንኛውም የሥጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ መንገደኞች እና ዕቃዎች ያለ ፍተሻ በቀጥታ እንዲያልፉ ይደረጋል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም  በመንገደኛው ወይም በዕቃው ላይ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር ወይም ለቁጥጥር ሲባል በአረንጓዴ የማለፊያ መስመር ከሚያልፉ መንገደኞች መካከል የሥጋት መገለጫዎች የሚታዩባቸውን መንገደኞች አልፎ አልፎ በሚደረግ መረጣ ከጠቅላላ መንገደኞች ውስጥ እስከ 5% የሚደርሱ መንገደኞች ላይ ድንገተኛ ፍተሻ ሊከናወን ይችላል፡፡
3) ማንኛውም የሥጋት ደረጃቸው ከፍተኛ የሆኑ መንገደኞች እና ዕቃዎች ፍተሻ ይደረግባቸዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 11. የኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤቶች የመንገደኞች እቃ የስራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት፤

1) በዚህ መመሪያ መሠረት ከመንገደኞች እና ከዕቃዎች ፍተሻ ጋር በተያያዘ የተገኙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያጠናቅራል፣ ተቋሙ ባዘጋጀው የመረጃ ማደራጃ ስርዓት (System)  ላይ ይመዘግባል በቀጣይም ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

2) በዚህ መመሪያ መሠረት በመንገደኞች እና በዕቃዎች ላይ የሥጋት ደረጃን በመጣል እንዲሁም በየወቅቱ ከሚከሰቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች በመነሳት ሌሎች የስጋት መስፈርቶችን በመለየት ተገቢውን አገልግሎት ይሰጣል።

3) በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው የሥጋት ደረጃ ለየት ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም ጥናት በማድረግ የሥጋት ደረጃዎች ማሻሻያ እንዲደረግ ግብአቶችን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል።

4) የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ የስጋት ደረጃዎች እንዲሻሻሉ ለባለስልጣኑ ያቀርባል።

5) የተለያዩ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም ለመንገደኞች መረጃ ይሠጣል።

12. <u>የታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ሃላፊነት</u>

ዳይሬክቶሬቱ ከቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በየጊዜው በሚደርሰው መረጃ መሰረት የማሻሻያ ሃሳቦችን ለስጋት ስራ አመራር ኮሚቴ /ለቻምፒዮንስ/ አቅርቦ ሲወሰን ለቅርንጫፍ ፅ/ቤቶቹ ማሻሻያው እንዲፈፀም ያስተላልፋል።

13. <u>የፍተሻ ኦፊሰሮች ሃላፊነት</u>

ማንኛውም የፍተሻ ኦፊሰር በዚህ መመሪያ መሰረት የሚደረግን ፍተሻ ሲያከናውን የመንገደኛውን ክብርና ስብእና በጠበቀ መልኩ እና ሌሎች የባለስልጣን መ/ቤቱን የስነምግባር ደንቦች ባከበረ መልኩ መሆን አለበት።

*14. <u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>*

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ------------------ ቀን 2006 ዓ.ም

በከር ሻሌ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር